https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፯
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 57
ADDIS ABABA 30th June, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፭/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ …ገጽ ፲፪ሺ፭፻፹፩

## Content

Proclamation No.1205/2020

Electronic Transaction Proclamation…..Page 12,581

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፭/፪ሺ፲፪

### የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽንን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

ወረቀትን እና ኮምፒዩተርን ማዕከል ያደረጉ ሰነዶችንና ኢንፎርሜሽኖችን የሚጠቀሙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በእኩል ሊያስተናግድ፣ እንደዚሁም ዜጎች፣ የግል ድርጅቶችና መንግሥታዊ ተቋሞች የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን እንዲጠቀሙ የሚያስችልና ይህን የሚያሳልጥ አስተማማኝ የሕግ ማዕቀፍ መፍጠር በማስፈለጉ፤

የኤሌክትሮኒክ ንግድን ጥቅም ላይ ማዋል የገበያ አማራጮቻችንን ስለሚያሰፋ፣ በዚህም ዜጎች በኢኮኖሚው ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ ኢትዮጵያ የዲጂታል ዘመንን እንድትቀላቀል ስለሚያስችል፤

የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎትን ሥራ ላይ ማዋል በየደረጃው ውጤታማ፣ ተጠያቂና ሁሉን ያቀፉ መንግሥታዊ ተቋሞችን በመገንባት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ጠቃሚ ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### PROCLAMATION No. 1205/2020

### PROCLAMATION TO PROVIDE FOR ELECTRONIC TRANSACTIONS

WHEREAS, it is necessary to provide equal treatment to users of paper and computer-based information; thereby creating a more secure legal environment, which enables and facilitates the use of electronic transactions by citizens and private entities, and public bodies;

WHEREAS, using electronic commerce positively affects market opportunities, thereby empowering citizens to be included in the economy, and also enable Ethiopia to be part of the digital era;

WHEREAS, deploying electronic government service in support of good governance is essential for building effective, accountable and inclusive institutions at all levels;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

https://chilot.me



## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፭/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "መልዕክት ተቀባይ" ማለት የመሐል አገናኞችን ሳይጨምር መልዕክቱን እንዲቀበል በአመንጪው የተወሰነ ሰው ነው፤

፪/ "ዶሜን" በአንድ ምድብ የሚካተት የኔትወርክ አካል አደራሻ መለያ ስም ነው፤

፫/ "የኮምፒዩተር ኮድ" ማለት አንድ የኮምፒዩተር ሥርዓት ተግባሩን እንዲያከናውን ወይም የታሰበውን ውጤት እንዲያስገኝ የሚያስችል በቃላት፣ በኮድ ወይም በዘዴ የሚገለፅ የመመሪያ ወይም የትዕዛዝ ስብስብ ነው፤

፬/ "ሶርስ ኮድ" ማለት በጽሁፍ የተቀመጠ በሰው ሊነበብ የሚችል ወደ ማሽን ተነባቢነት ያልተቀየረ የኮምፒዩተር ኮድ ወይም ፕሮግራም ማለት ነው፤

፭/ "ኦብጀክት ኮድ" ማለት ምንጪ ኮድን በግብዓትነት ለመውሰድ እና አቀናባሪ በመጠቀም ወደማሽን ተነባቢነት የተቀየረ የኮምፒዩተር ኮድ ማለት ነው፤

፮/ "አልጎሪዝም" ማለት ስልተ ቀመር ሲሆን ስልተ ቀመር ማለት አንድን ችግር ለመፍታት የምንከተለው ቅደምተከተል ነው፤

፯/ "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤

፰/ "ኮሙኒኬሽን" ማለት የውል አቀራረብና አቀባበልን ጨምሮ ሰዎች ከኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን ጋር በተያያዘ የሚወስኗቸው ወይም ለውሳኔ የሚመርጧቸው ትዕዛዞች፣ ማስጠንቀቂያዎች፣ ጥያቄዎች፣ ወይም መሰል መልዕክቶች ናቸው፤

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Electronic Transaction Proclamation No. 1205/2020".

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context requires otherwise,:

1/ "addressee" means the person determined by the originator to receive the communication but does not include an intermediary;

2/ "Domain" means the part of a network address that identifies it as belonging to a particular domain.

3/ "computer Code" = a set of instructions or commands expressed in words, codes or schemes which are capable of causing a computer system to perform or achieve a particular task or result;

4/ **Source code** is a computer code in the form of text used to express instructions at a high-level that is human readable and note yet converted to a machine readable format

5/ Object code is a computer code which is the output from a compiler that has compiled said source code.

6/ Algorithm : A rule or procedure for solving a problem.

7/ "Authority" means the Ethiopian Communication Authority;

8/ "communication" means any command ,notice or request or similar messages including an offer and the acceptance of an offer that a person is required to make or chooses to make in connection with an electronic transaction;

https://chilot.me



፱/ “የኮሙኒኬሽን ኔትዎርክ አገልግሎቶች” ማለት የኮሙኒኬሽን መስመሮችን ማቅረብ፣ ለኮሙኒኬሽን ሥርዓት የሚውሉ ግብዓቶችን ማንቀሳቀስ፣ የኮሙኒኬሽን ሥርዓቶችን ተደራሽ ማድረግ፣ ተገልጋይ በለያቸው የመዳረሻ ወይም የመተላለፊያ ነጥቦች መካከል ኢንፎርሜሽን ማስተላለፍ፣ ዳታ መተንተንና ማከማቸት ነው፤

፲/ “የዳታ መልዕክት” ማለት በኤሌክትሮኒክ፣ በማግኔታዊ፣ በኦፕቲካል ወይም በሌላ ተመሳሳይ መንገድ የመነጨ፣ የተላከ፣ የደረሰ ወይም የተከማቸ ኢንፎርሜሽን ነው፤

፲፩/ “ኤሌክትሮኒክ” ማለት ከቴክኖሎጂ አንጻር የኤሌክትሪክ፣ የማግኔታዊ፣ የኦፕቲካል ወይም ሌላ ተመሳሳይ አቅም ያለው የመጠቀሚያ መንገድ ነው፤

፲፪/ “የኤሌክትሮኒክ ንግድ” ማለት ኢንተርኔትን ወይም ሌሎች የመረጃ መረብን በመጠቀም የሚደረግ የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ግብይት ወይም ልውውጥ ነው፤

፲፫/ "የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሽ" ማለት በኢንተርኔት ወይም በሌላ የመረጃ መረብ አማካኝነት ሸቀጦችን በመሸጥ ወይም አገልግሎቶችን በማቅረብ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

፲፬/ "የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሽ" ማለት በኤሌክትሮኒክ ንግድ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በራሳቸው የንግድ ሥራ ለማካሄድ እንዲችሉ ቀጥታ ተደራሽ የሆኑ ድረገጾችን የሚያቀርብ፣ የሚያቀራርብ፣ ኢንፎርሜሽን የሚለቅና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚሰጥ ድርጅት ነው፤

፲፭/ "ኤሌክትሮኒክ ሰነድ" ማለት በኤሌክትሮኒክ ቅርጽ ያለ ሰነድ፣ መዝገብ፣ ኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን ወይም ትራንዛክሽን ነው፤

፲፮/ "ኤሌክትሮኒክ መልዕክት" ማለት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ዘዴዎች አማካኝነት የመነጨ፣ የተላከ፣ የደረሰ ወይም የተከማቸ ኢንፎርሜሽን ነው፤

9/ “communication network services” means provision of connections, the operation of facilities for communication systems, the provision of access to communication systems, transmission or routing of data messages between or among points specified by a user and the processing and storage of data;

10/ “data message” means information generated, sent, received or stored by electronic, magnetic, optical or other similar means ;

11/ “electronic” means the technology of utilizing electrical, magnetic, optical, electromagnetic, or similar capacities regardless of the medium;

12/ “electronic commerce” means transaction of goods and services through the Internet or other information networks;

13/ “electronic commerce operator” means a person that engages in the business activities of selling commodities or providing services through the Internet or other information network;

14/ “electronic commerce platform operator” means legal entities who, in electronic commerce, provide two or multiple parties with online sites for business operations, match-making, information release and other services, for the latter to carry out trading activities independently;

15/ “electronic document” means document, record, information, communication or transaction in electronic form;

16/ “electronic message” means information and electronic document created, sent, received, or stored by electronic means or any other similar means;

https://chilot.me



፲፯/ "ኤሌክትሮኒክ መዝገብ" ማለት በኤሌክትሮኒክ መንገድ የመነጨ፣ የተከማቸ፣ የደረሰ ወይም የተሰራጨ የጽሑፍ ሰነድ ወይም መዝገብ ነው፤

፲፰/ "ኤሌክትሮኒክ ፊርማ" ማለት ከኤሌክትሮኒክስ መልዕክት ጋር በተያያዘ ፈራሚውን ለመለየትና በኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ውስጥ የተካተተው ኢንፎርሜሽን በፈራሚው የጸደቀ ወይም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ለማመልከት ጥቅም ላይ የሚውል በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ውስጥ ያለ፣ በኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ላይ የተለጠፈ ወይም ከኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ጋር ምክንያታዊ በሆነ አኳኋን የተቆራኘ በኤሌክትሮኒክ መልክ ያለ ኢንፎርሜሽን ነው፤

፲፱/ "ኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን" ማለት ተንቀሳቃሽ ስልክንና ሌሎች መሰል መሣሪያዎችን ጨምሮ በኮምፒውተር በታገዘ የኢንፎርሜሽን መረብ ሥራን ማከናወን ሲሆን፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድንና የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎትን ይጨምራል፤

፳/ "ዶት ኢቲ ዶሜይን ስም ቦታ" ማለት በአይኤስኦ 3166-1 ዓለምአቀፍ ደረጃዎች በተደረገው ምደባ መሠረት የኢንተርኔት ሥርዓት ከፍተኛ ደረጃ በሆነው የባለሁለት ፊደል ኮዶች መሠረት ለኢትዮጵያ ተለይቶ የተሰጠ የዶት ኢቲ የአገር መለያ ከፍተኛ ደረጃ ዶሜይን ነው፤

፳፩/"ኢንፎርሜሽን" ማለት ጽሁፍን፣ መልዕክትን፣ ዳታን፣ ድምጽን፣ የዳታ ቋትን፣ ቪዲዮን፣ ምልክቶችን፣ ሶፍትዌርን፣ የኮምፒዩተር ፕሮግራሞችን፣ ኦብጀክት ኮድንና ሶርስ ኮድን ይጨምራል፤

፳፪/"የኢንፎርሜሽን ሥርዓት" ማለት ኢንፎርሜሽን የሚያመነጭ፣ የሚልክ፣የሚቀበል፣ የሚያከማች፣ ወይም በሌላ መንገድ የሚተነትን ሥርዓት ነው፤

፳፫/"የመሐል አገናኝ" ማለት አንድን ሰው በመወከል የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን የሚልክ፣ የሚቀበል፣ የሚያከማች፣ ወይም ከኤሌክትሮኒክ መልዕክት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች አገልግሎቶችን የሚያቀርብ ሰው ነው፤

17/ "electronic record" means a written document, or other record generated, stored, received, or communicated by electronic means;

18/ "electronic signature" means information in electronic form in, affixed to or logically associated with, an electronic message, which may be used to identify the signatory in relation to the data message and to indicate the signatory's approval of the information contained in the data message;

19/ "electronic transaction" means the conducting of businesses over computer mediated networks including mobile phones and other devices, and shall include, but is not limited to, electronic commerce and electronic government services;

20/ ".et domain name space" means .et Country Code Top Level Domain which is the top level of the Internet domain name system assigned according to the two-letter codes in the International Standard ISO 3166-1 to Ethiopia;

21/ "information" shall include text, message, data, voice, sound, database, video, signals, software, computer programs, including object codes and source codes;

22/ "information system" means a system for generating, sending, receiving, storing or otherwise processing information;

23/ "intermediary" means a person, who, on behalf of another person, sends, receives or stores such an electronic message or provides other services with respect to that electronic message;

https://chilot.me


፳፬/"መካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሽ" ማለት በኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አማካኝነት ሸቀጦችን የሚሸጡ ወይም አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾችን በተለያየ ማዕቀፍ አደራጅቶ የሚይዝ ድርጅት ነው፤

፳፭/"ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፳፮/"አመንጪ" ማለት በራሱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት የኤሌክትሮኒክ መልዕክት የላከ ወይም እንዳግባቡ ከማከማቸቱ በፊት ያመነጨ ሲሆን፣ በኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ዙሪያ ያሉ የመሐል አገናኞችን አይጨምርም፤

፳፯/"ምዝገባ" ማለት የዶሜይን ስም ምዝገባ አገልግሎት አቅራቢዎችንና የዶሜይን ስሞችን የሚመለከቱ ሌሎች ኢንፎርሜሽኖችን ለማከማቸትና መልሶ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥርዓት ነው፤

፳፰/"የደህንነት ሥርዓት" ማለት

ሀ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ወይም የኤሌክትሮኒክ ፊርማ የአንድ የተወሰነ ሰው መሆኑን ማረጋገጥ፣ ወይም

ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች ሲሰራጩ፣ ይዘታቸው ወይም ክምችታቸው ላይ የሚታዩ ግድፈቶችና ለውጦችን አልጎሪዝም እና ኮዶችን በመጠቀም፣ ቃላቶችን ወይም ቁጥሮችን በመለየት፣ የመመስጠሪያ ወይም የታወቁ ሂደቶችንና መሰል መሳሪያዎችን በመጠቀም የመልዕክቶችን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት ነው፤

፳፱/"ፈራሚ" ማለት የፊርማ መፍጠሪያ ዳታ የያዘ፣ እና በራሱ ወይም ሌላውን ሰው ወክሎ የሚሠራ ሰው ነው፤

፴/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፴፩/ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ይጨምራል።

24/ "intra-platform operator" means an entity which aggregates electronic commerce operators that sell commodities or provide services through an electronic commerce platform in different categories;

25/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or the Minister of Innovation and Technology; respectively;

26/ "originator" means a person by whom, or on whose behalf, the electronic message has been sent or generated prior to storage, if any, but it does not include a person acting as an intermediary with respect to that electronic message;

27/ "registry" means a system for registering domain name registration service providers, and for storing and retrieving other information relating to domain names;

28/ "security procedure" means a procedure for the purpose of :

a) verifying that an electronic message or electronic signature is that of a specific person; or

b) detecting an error or alteration in the communication, content or storage of an electronic message from a specific period of time, which requires the use of algorithms or codes, identifying words or numbers, encryption or known procedures and similar devices for originality of messages;

29/ "signatory" means a person who holds signature creation data and who acts either on his own behalf or on behalf of the person he represents;

30/ person" means a physical or legal person;

31/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

https://chilot.me



**፫. የአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን**

፩/ ይህ አዋጅ፡-

ሀ) ለሕዝብ አገልግሎት የመስጠት ሥልጣንና ተግባር ባላቸው የፌደራል እና የክልል መንግሥታት፣የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደር ተቋማት ላይ እና፤ እንደዚሁም

ለ) በኤሌክትሮኒክ ንግድ፣ በኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎት፣ በኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች፣ በዶት ኢ.ቲ የዶሜይን ስም አስተዳደር፣ እና በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ፤

ተፈጻሚ ነው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ፡-

ሀ) ጋብቻና ፍቺን ጨምሮ ከግላዊ ሁኔታ ጋር ከተዛመዱ ጉዳዮች፤

ለ) ከኑዛዜ መስጠት፣ ከኑዛዜ ፎርሞች፣ ኑዛዜን ከመሻር፣ እና ከውርስ አፈጻጸም ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች፤

ሐ) ከፍርድ ቤት ትዕዛዞች፣ መጥሪያዎች፣ የብርበራና የመያዣ ትዕዛዞች እና ሌሎች መሰል ውሳኔዎች፤

መ) የማይንቀሳቀስ ንብረትን ከማስተለለፍ ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች፤ እና

ሠ) ከህጋዊ የውክልና ጉዳዮች፤

ጋር በተያያዘ ጽሁፍን ወይም የእጅ ፊርማን እንደ ግዴታ በሚወስዱ ማናቸውም ሕጎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

**3. Scope of Application**

1/ This Proclamation shall apply:

a) on institutions of the Federal and Regional Governments, and the City Administration of Addis Ababa and Diredawa which have the power and function to provide services to the public, and

b) electronic commerce, electronic government service, electronic messages, <.et> domain name administration and related subjects.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article this Proclamation shall not apply to any law requiring writing or signatures for the following matters:

a) transactions and matters related to personal status such as marriage and divorce;

b) transactions related to the making, execution or revocation of a will or testamentary instrument;

c) court procedures, judicial summons, search orders, arrest orders and judicial decrees;

d) transactions related to the transfer of any interest in immovable property; and

e) the creation, performance or enforcement of power of attorney.

**፬. የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አስገዳጅ አለመሆኑ**

ማንኛውም ሰው ፈቃደኝነቱን እስካልሰጠ ድረስ በማንኛውም የንግድ እንቅስቃሴ ወይም ከመንግሥት ተቋማት ጋር ባለው ግንኙነት የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን እንዲጠቀም፣ እንዲያቀርብ ወይም እንዲቀበል አይገደድም።

**4. Use not Mandatory**

Nothing shall make it mandatory for a person to use, provide or accept any electronic message in any commercial transaction or dealings with government bodies unless the person consents to the using, providing or accepting of the electronic message.

https://chilot.me



**፭. የተቆጣጣሪ ተቋሞች ኃላፊነትና ተግባር**

፩/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ ይፈጽማል፤ያስፈጽማል፤ ለአዋጁ ተፈጻሚነት ሌሎች መንግሥታዊ እና የግል ተቋሞችን ያስተባብራል፣ ይመራል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተደነገጉ ተግባሮችን እና ኃላፊነቶችን ለመፈጸም ሚኒስቴሩ፡-

ሀ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የብቃት ደረጃዎችን፤

ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ኮሙኒኬሽንን፤

ሐ) የመሐል አገናኞች የተጠያቂነት ገደብን፤

መ) የሸማቾች መብት ጥበቃን፤

ሠ) የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች፤

ረ) የፌዴራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብን፤

ሰ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክት አመራር እና አጠባበቅ፤

ሸ) ዳታን ወደ ኮምፒውተር የማስገባትና የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን የማረጋገጫ ዘዴዎችን፤ እንደዚሁም

ቀ) እንዳስፈላጊነቱ በየጊዜው በሚወሰኑ ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ፤

መመሪያዎችን ያወጣል።

፫/ የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን በዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና ሌሎች ሕጎች መሠረት የዶት ኢቲ የዶሜይን ስም ቦታን የመምራትና የማስተዳደር ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል።

**፮. የብሔራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ካውንስል መቋቋም**

፩/ በዚህ አዋጅ የብሔራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ምክር ቤት ተቋቁሟል።

**5. Regulatory Authorities and their Powers and Functions**

1/ The Ministry shall execute, and cause to be executed this Proclamation; it shall also coordinate and lead government and private entities for the implementation of this Proclamation.

2/ In performing the powers and functions stipulated under Sub-Article (1) of this Article, the Ministry shall in particular issue directives on the following:

a) information technology standards;

b) communication of electronic messages;

c) limitations on the liabilities of intermediaries;

d) consumer protection;

e) electronic government services;

f) federal electronic register of laws;

g) management and maintenance of the electronic message;

h) methods relating to data entry and verification of the electronic message; and

i) any other matters as may be required from time to time.

3/ Ethiopian Communication Authority shall have the powers and functions, as per the pertinent parts of this Proclamation, regulations thereto, and any other law, to administer and manage the <.et> domain name space.

**6. Establishment of the National Digital Economy Council**

1/ The National Digital Economy Council is hereby established by this Proclamation.

https://chilot.me



፪/ የምክር ቤቱ አባላት ሚኒስትሩን ጨምሮ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።

፫/ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማል፤ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት በውስጡ ያደራጃል፡፡

፬/ ካውንስሉ የኤሌክትሮኒክ ግብይት እና የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶችን ጨምሮ በዲጂታል ኢኮኖሚ ዙሪያ መንግሥትን የማማከር ሚና አለው።

፭/ ካውንስሉ አግባብነት ካላቸው ከተለያዩ የመንግሥት ተቋማት የተውጣጡ የሥራ ቡድኖች ሊያቋቋም ይችላል።

2/ Members of the Council including the Minister shall be appointed by the Prime Minister and their number shall be determined as necessary

3/ The chair of the Council shall be assigned by the Prime minister; The ministry shall organize the office of the council..

4/ The Council shall advice the government on, including electronic commerce and electronic government service, the Digital Economy.

5/ The Council may establish different working groups with members drawn from relevant government institutions.

## ክፍል ሁለት
## የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች
### ንዑስ ክፍል አንድ
### ሕጋዊ መስፈርቶች

## PART TWO
## ELECTRONIC MESSAGES
### SUB-SECTION ONE
### LEGAL REQUIREMENTS

**፯. ሕጋዊ ውጤት**

፩/ ኢንፎርሜሽን በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ይዘት መቅረቡ ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው አያደርግም።

፪/ ኢንፎርሜሽን በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ውስጥ ተካቶ አለመቅረቡና ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ባደረገው በዚህ መልዕክት ውስጥ መጠቀሱ ኢንፎርሜሽኑ ለተላከለት ሰው ተደራሽ መሆን የሚችል ከሆነ ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው አያደርግም።

**7. Legal Outcome**

1/ Information shall not be denied legal effect solely on the ground that it is in the form of an electronic message.

2/ Information shall not be denied legal effect solely on the grounds that it is not contained in the electronic message that gives rise to such legal effect, but is merely referred to in that electronic message, provided that the information being referred to is accessible to the person against whom the referred information might be used.

**፰. ጽሁፍ**

ማንኛውም ኢንፎርሜሽን በጽሁፍ እንዲቀርብ በሕግ ግዴታ ከተጣለ ይህ ኢንፎርሜሽን በኤሌክትሮኒክ መልክ ከቀረበ ወይም ከተቀመጠ፣ ተደራሽ ከሆነ፣ እና በቀጣይ ለማመሳከሪያነት መዋል የሚችል ከሆነ የኢንፎርሜሽኑን አቀራረብ አስመልክቶ የተጠየቀው ቅድመ ሁኔታ እንደ ተሟላ ይቆጠራል።

**8. Writing**

Where the law requires information to be in writing, that requirement is met by an electronic message if the information contained therein is rendered or made available in an electronic form; is accessible; and is capable of being retained for subsequent references.

https://chilot.me



## ፱. ፊርማ

፩/ ማንኛውም ሰነድ ፊርማ እንዲያርፍበት በሕግ ግዴታ ከተጣለ እና የትኛው ፊርማ ተቀባይነት እንዳለው ሕጉ ካልገለጸ፣ በኤሌክትሮኒክስ የቀረበው ፊርማ በሕግ የተጠቀሰው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ የሚቆጠረው፦

ሀ) የግለሰቡን ማንነት ለመለየት እና በኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ውስጥ የተካተተው ኢንፎርሜሽን በግለሰቡ የጸደቀ መሆኑን የሚያመላክት ዘዴ ጥቅም ላይ ከዋለ፤ እና

ለ) ዘዴው ስምምነትን ጨምሮ ያሉ ሌሎች ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ለመነጨበት ወይም ለተሰራጨበት ዓላማ አስተማማኝና ተስማሚ ሆኖ ከቀረበ፤

ብቻ ነው።

፪/ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አስተማማኝ ነው የሚባለው፦

ሀ) ጥቅም ላይ በዋለበት አግባብ፣ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ መፍጠሪያ ዘዴዎቹ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሳይሆን ከፈራሚው ጋር የተቆራኘ ከሆነ፤

ለ) ፊርማው በሚፈረምበት ወቅት፣ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ መፍጠሪያ ዘዴዎቹ በሌላ በማንኛውም ሰው ሥር ሳይሆን በራሱ በፈራሚው ቁጥጥር ሥር የነበሩ፣ እና ከግዳጅና ካላስፈላጊ ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ የተፈረመ ከሆነ፤ እና

ሐ) የኤሌክትሮኒክ ፊርማው ከተፈረመ በኋላ የተደረገ ማንኛውም ለውጥ ወይም ማሻሻያ በቀላሉ ሊደረስበት የሚችል ከሆነ፤

ብቻ ነው።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የአንድን ሰው የኤሌክትሮኒክ ፊርማን ትክክለኛነት ወይም ትክክለኛ አለመሆን በማንኛውም ሕጋዊ መንገድ ማረጋገጥ ይቻላል፣

፬/ በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን ፊርማን አስመልክቶ በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 9. Signature

1/ Where the signature of a person is required by law and such law does not specify the type of signature, that requirement in relation to an electronic message is met only if:

a) a method is used to identify that person and to indicate that person's approval of the information contained in the electronic message; and

b) that method is as reliable as was appropriate for the purpose for which the electronic message was generated or communicated, in the light of all the circumstances, including any relevant agreement.

2/ An electronic signature shall be considered reliable if:

a) the means of creating the electronic signature is, within the context in which it is used, linked to the signatory and not any other person;

b) the means of creating the electronic signature was, at the time of signing, under the control of the signatory and not any other person and was done without duress and undue influence; and

c) any alteration made to the electronic signature after signing is detectable.

3/ Sub-Article (2) of this Article does not limit the right of a person to prove the authenticity of an electronic signature in any other lawful way;

4/ The Electronic Signature Proclamation shall apply to any signature in any electronic transaction which is not covered by this Proclamation.

https://chilot.me



፲. **ማህተም**

ሕግ በሰነድ ላይ ማሕተም እንዲያርፍ ግዴታ ከጣለ ሰነዱ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ቅርጽ ከቀረበና በኤሌክትሮኒክ ፊርማ መሠረት የዲጂታል ፊርማ ካረፈበት በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል።

፲፩. **እማኝ**

ሕግ በሰነድ ላይ የእማኞች ፊርማ እንዲያርፍ ግዴታ ከጣለ፣ ሰነዱ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ቅርጽ ከቀረበ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ የተቀመጠው መሥፈርት የሚያሟላ የምስክር የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ካረፈበት በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል።

፲፪. **ዋና ቅጅ**

፩/ ሕግ ኢንፎርሜሽን በዋና ቅጅ እንዲቀርብ ወይም እንዲቀመጥ ግዴታ ከጣለ፦

ሀ) ኢንፎርሜሽኑ የመጨረሻውን ቅርጽ ይዞ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ወይም በሌላ መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመነጨበት ጊዜ አንስቶ ያለመቀየሩን የሚያሳይ አስተማማኝ ዋስትና ካለ፣ እና

ለ) ኢንፎርሜሽኑ በማንኛውም በተፈለገ ጊዜ ጥቅም ላይ ከማዋል አኳያ ተደራሽና የሚነበብ ከሆነ፣

የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ይህን ቅድመ-ሁኔታ እንዳሟላ ይቆጠራል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ያልተቀየረ መሆኑ የሚመዘነው፦

ሀ) ከኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን፣ ክምችትና ማሳየት ጋር በተያያዘ ከሚጨመሩ ወይም ከሚመነጩ ለውጦች ውጪ ኢንፎርሜሽኑ ምሉዕና ያልተለወጠ ሆኖ መቆየቱን በማገናዘብ፣

ለ) ኢንፎርሜሽኑ የመነጨበት ዓላማን በመመልከት፣ እና

ሐ) ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

10. **Seal**

Where a law requires a seal to be affixed to a document, the requirement of the law is fulfilled, if the document is in the form of an electronic message, by a digital signature as provided under the Electronic Signature Proclamation.

11. **Witness**

Where a law requires the signature of a witness on a document, the requirement of the law is fulfilled, if the document is in the form of an electronic message, by an electronic signature of the witness that complies with the requirements of Article 9 of this Proclamation.

12. **Original Copy**

1/ Where a law requires information to be presented or retained in its original form, that requirement is met by an electronic message if:

a) there exists a reliable assurance as to the integrity of the information from the time when it was first generated in its final form, as an electronic message or otherwise; and

b) if the information can be accessible and intelligible so as to be usable at any time as may be required.

2/ For the purposes of Sub-Article (1) paragraph (a) of this Article, integrity must be assessed:

a) by considering whether the information has remained complete and unaltered, except for the addition of any endorsement and any change which arises in the normal course of communication, storage and display;

b) in the light of the purpose for which the information was generated; and

c) having regard to all other relevant circumstances.

https://chilot.me



## ፲፫. ተቀባይነት እና የማስረጃ ክብደት

፩/ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች በማንኛውም የሕግ ሂደቶች ተቀባይነት አላቸው፤ እንደ ማስረጃም ያገለግላሉ።

፪/ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ የማስረጃ ክብደት ሲመዘን፦

ሀ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ የመነጨበት፣ የተከማቸበት ወይም የተሰራጨበት አግባብ አስተማማኝነት፤

ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ይዘት ሳይቀየር የቆየበት መንገድ አስተማማኝነት፤

ሐ) የመልዕክቱ አመንጪ ተለይቶ የታወቀበት መንገድ፤ እና

መ) ፍርድ ቤት አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያስቀምጣቸው ሌሎች እውነታዎች፤

ግምት ውስጥ ይገባሉ።

## ፲፬. ማስቀመጥ

፩/ በሕግ ሰነዶች፣ መልዕክቶች እና ኢንፎርሜሽን እንዲቀመጡ ግዴታ ከጣለ በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ የሚቆጠረው፦

ሀ) በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ውስጥ የሚገኝ ኢንፎርሜሽን ተደራሽ እና በቀጣይ ለማመሳከሪያነት መዋል የሚችል ከሆነ፤

ለ) ኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ በተቀረጸበት፣ በተላከበት፣ በደረሰበት ጊዜ በመነሻ የነበረውን ይዘት ጠብቆ ከቆየ ወይም የመልዕክቱ ይዘት ያልተለወጠ መሆኑን ማሳየት የሚቻል ከሆነ፤ እና

ሐ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ላኪና ተቀባዩን፣ የተላከበትን ወይም የደረሰበትን ቀንና ሰዓትን ማወቅ የሚያስችል ከሆነ ነው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) በተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎች ዙሪያ ሶስተኛ ወገኖች የሚሰጧቸው አገልግሎቶች እንደ በቂ ይቆጠራሉ።

## 13. Admissibility and Evidential Weight

1/ In any legal proceedings, electronic messages shall be accepted and is admissible as evidence.

2/ In assessing the evidential weight of an electronic message, regard shall be placed on:

a) the reliability of the manner in which the electronic message was generated, stored or communicated;

b) the reliability of the manner in which the integrity of the electronic message was maintained;

c) the manner in which its originator was identified; and

d) any other relevant fact the court may consider relevant.

## 14. Retention

1/ Where a law requires that documents, messages and information be retained, that requirement shall be satisfied by an electronic message provided that if the following conditions are met:

a) the information contained in the electronic message is accessible and is capable of retention for subsequent reference;

b) is retained in the format in which it was generated, sent, received, or in the format that can demonstrate that the contents were not altered; and

c) if the origin and receiver of the electronic message, and the date and time when it was sent or received can be determined.

2/ The requirements referred to in Sub-Article (1) of this Article are satisfied by using the services of a third party.

https://chilot.me



፫/ ሕግ ወረቀትን ማዕከል ያደረጉ ሰነዶችና መረጃዎች ለተወሰኑ ዓመታቶች እንዲቆዩ የጣለው ግዴታ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) በተጠቀሱ ሰነዶች፣ መዝገቦችና ኢንፎርሜሽን ላይ ተፈጻሚ ነው።

፬/ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ሰነዶች፣ መልዕክቶች ወይም ኢንፎርሜሽን እንዲቀመጡ የተጣለው ግዴታ መልዕክቶችን ለመላክ ወይም ለመቀበል ሲባል ብቻ ጥቅም ላይ በዋሉ መልዕክቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

## ፲፭. ቅጅ እና አፃፃፍ

፩/ በሕግ ሰነዶች ከአንድ በላይ በሆኑ ቅጂዎች መቀመጥ፣ መቅረብ፣ መላክ ወይም መስጠት አለባቸው በማለት ከደነገገ፤ ሰነዱ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ከተቀመጠ፣ ከቀረበ፣ ከተላከ ወይም ከተሰጠ በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደ ተሟላ ይቆጠራል።

፪/ በሕግ ሰነዶች በታዘዘው አፃፃፍ እንዲቀርቡ ከደነገገ፣ የኤሌክትሮኒክ መልዕክት የሆነ ሰነድ በሕግ የተደነገገውን ቅድመ ሁኔታ አሟልቷል የሚባለው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ፦

ሀ) ከታዘዘው ቅርጽ ጋር ተመሳሳይ ወይም በአብዛኛው ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ፎርማት የተደረገ ከሆነ፤

ለ) በቀጣይ ለማመሳከሪያነት መዋል እንዲችል ተደራሽና ሊነበብ የሚችል፤ እና

ሐ) ሌላ ሰው ጋር ሊቀመጥ የሚችል ከሆነ ነው።

## ፲፮. ክፍያ እና ደረሰኝ

፩/ ክፍያ እንዲፈፀም የሚጠይቅ ትራንዛክሽን ክፍያው በኤሌክትሮኒክ መንገድ ከተፈፀመና አግባብነት ያለው የመንግሥት ተቋም ያስቀመጣቸው ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል። አግባብነት ያለው የመንግስት ተቋም የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፡፡

፪/ ሕግ የክፍያ ደረሰኝ እንዲሰጥ ግዴታ የሚጥል ከሆነ በሕግ የተቀመጠው ግዴታ እንደ ተሟላ የሚቆጠረው፦

3/ A document, record or information referred to in Sub-Articles (1) and (2) shall be kept in electronic form for at least the number of years a corresponding paper based document is required by law to be retained.

4/ The obligation to retain documents, messages or information in accordance with the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall not apply to any document the sole purpose of which is to enable the message to be sent or received.

## 15. Copy and Prescribed Form

1/ Where a law requires any document to be retained, served, sent or delivered in more than one copy, the requirement of the law is fulfilled, if the document is in the form of an electronic message, by retention, service, sending or delivery of the document in one copy.

2/ Where a law requires any document to be in a prescribed form, the requirement of the law is fulfilled by a document in the form of an electronic message if the electronic message is:

a) formatted in the same or substantially the same way as the prescribed form;

b) accessible and intelligible so as to be usable for subsequent reference; and

c) capable of being retained by the other person.

## 16. Payment and Receipt

1/ Where a transaction requires any payment to be made, the requirement of the law is fulfilled if the payment is made by an electronic means and complies with any condition imposed by the relevant government body. The relevant government body may issues implementing directive.

2/ Where a law requires the issuance of any receipt of payment, the requirement of the law is fulfilled if:

https://chilot.me



ሀ) ደረሰኙ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ቅርጽ የተዘጋጀ፤

ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ የወረቀት ደረሰኝ ይዘትን የሚያሟላ፤ እንደዚሁም

ሐ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ በቀጣይ ለማመሳከሪያነት መዋል እንዲችል ተደራሽና ሊነበብ የሚችል፤

ከሆነ ነው።

## ፲፯. ስለውል አመሠራረት

ከውል አመሠራረት ጋር በተያያዘ ተዋዋይ ወገኖች ከዚህ በተቃራኒ ካልተስማሙ በስተቀር፤ የውል አቀራረብ፣ የውል አቀባበል፣ የውል አቀራረብ ቀሪ መሆን፣ የውል አቀባበል ቀሪ መሆን፣ ወይም ሌሎች የመረጃ ልውውጦች በሙሉ ወይም በከፊል በኤሌክትሮኒክ መንገድ ሊገለፁ ይችላሉ።

## ፲፰. ሕጎችን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማተም

ሕግ እንዲታተም ግዴታ ከተጣለ ሕጉ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ከታተመ በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ ይቆጠራል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ኮሙኒኬሽን

## ፲፱. የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ምንጭ

፩/ የኤሌክትሮኒክ መልዕክት፡-

ሀ) በራሱ በአመንጪው፤

ለ) አመንጪውን እንዲወክል ሥልጣን በተሰጠው ሰው፤ ወይም

ሐ) የአውቶማቲክ ሥርዓቱ ፕሮግራም በተደረገው መሠረት አለመሥራቱ ካልተረጋገጠ በስተቀር፤ መልዕክት በራሱ ጊዜ እንዲልክ ተደርጎ ፕሮግራም በተደረገ የአውቶማቲክ ሥርዓት አማካይነት የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ በራሱ በአመንጪው ወይም በተወካዩ አማካይነት፤

የተላከ ከሆነ የአመንጪው ነው ተብሎ ይወሰዳል።

a) the receipt is in the form of an electronic message;

b) the electronic message fulfills all the elements of a paper-based receipt; and

c) the electronic message is accessible and intelligible so as to be usable for subsequent reference.

## 17. Formation of Contracts

In the context of contract formation, unless otherwise agreed by the parties, an offer, the acceptance of an offer, the revocation of an offer, the revocation of an acceptance, or any related communication may be wholly or partly expressed by means of electronic message.

## 18. Electronic Publication of Laws

Where the law requires that a law shall be published, the requirement of the law is fulfilled if it is published electronically.

## SUB-SECTION TWO
## COMMUNICATION OF ELECTRONIC MESSAGES

## 19. Origin of Electronic Message

1/ An electronic message shall be attributable to the originator where:

a) it is sent by the originator personally;

b) it is sent by a person who is authorized to represent the originator; or

c) the electronic message is sent through an automatic system programmed by the originator or its representative unless it is proved that the automatic system did not properly execute such programming.

https://chilot.me



፪/ የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ተቀባዩ መልዕክቱ የተላከው ከአመንጪው ነው ብሎ ግምት የሚወስደው፡-

ሀ) መልዕክቱ ከኢንፎርሜሽን አመንጪው የተላከ መሆኑን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል ስምምነት የተደረሰበት አሠራር ጥቅም ላይ ከዋለ፣ ወይም

ለ) መልዕክቱ ከአመንጪው ወይም ከወኪሉ ጋር ያለው ግንኙነት፣ አመንጪው የሚልካቸው መልዕክቶች የእርሱ እንደሆኑ የሚያሳዩ ዘዴዎችን እንዲያገኝ የተመቻቸለት ሰው ከፈጸማቸው ተግባሮች የመጣ ከሆነ ነው።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው ቢኖርም፣ ከሌሎች ምክንያቶች ባሻገር፡-

ሀ) የመልዕክቱ ተቀባይ መልዕክቱ ከአመንጪው የተላከ እንዳልሆነ በጊዜ እንዲያውቅ የተደረገ፣ እና መልዕክት ተቀባዩ እርምጃ ለመወሰድ የሚያስችል በቂ ጊዜ የተሰጠው ከሆነ፣ ወይም

ለ) መልዕክት ተቀባዩ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ወይም በአመንጪውና በእርሱ መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት የማረጋገጫ ዘዴ በመከተል፣ መልዕክቱ ከአመንጪው እንዳልሆነ ካወቀ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት መንገድ ካለ፣

የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ሕጋዊ ውጤት የለውም።

፬/ መልዕክት ተቀባዩ መልዕክቱ የመጀመሪያው መልዕክት ቅጅ መሆኑን ካወቀ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት ሁኔታ ከሌለ በስተቀር፣ እያንዳንዱን የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን ራሱን የቻለ አዲስ መልዕክት አድርጎ መቁጠርና ለዚህም ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል።

## ፳. <u>መልዕክት ስለመድረሱ የሚሰጥ ማረጋገጫ</u>

፩/ መልዕክት አመንጪው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱን ስለመቀበሉ ማረጋገጫ እንዲሰጠው ተቀባዩን ሊጠይቅ ይችላል። የመልዕክት አመንጪው ማረጋገጫ የሚሰጥበትን ፎርም ለይቶ ካልወሰነ መልዕክት ተቀባዩ፡-

2/ The addressee of an electronic message may regard it as being that of the originator where:

a) an agreed procedure has been applied to recognize a message from the originator; or

b) the electronic message comes from the actions of a person whose relationship with the originator or any agent of the originator enabled that person to gain access to a method used by the originator to identify electronic messages as its own.

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article electronic message shall be considered invalid where. inter alias

a) the receiver of the message has been notified in time by the originator that the message is not his and had reasonable time to act accordingly; or

b) the addressee knew or had means to know that the electronic message is not from the originator had he exercised reasonable care or used any authentication method agreed between the originator and the addressee.

4/ The addressee has to regard each electronic message received as a separate new electronic message and to act on that assumption, except to the extent that he knew or was able to know that the electronic message is a duplicate of the first one.

## 20. <u>Acknowledgement of Receipt</u>

1/ The originator may request the addressee to acknowledge receipt of electronic message. Where the originator does not specify a particular form, the addressee may apply one of the following methods:

https://chilot.me



ሀ) አውቶሜትድ በሆነ ወይም በሌላ መንገድ ምላሽ በመስጠት፣ ወይም

ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱን ስለመቀበሉ አመንጪው እንዲረዳ የሚያደርግ ማናቸውም ተግባርን በመፈጸም መልዕክቱ ስለመድረሱ ሊያረጋግጥ ይችላል።

፪/ የመረጃ አመንጪው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው ከመልዕክት ተቀባዩ ማረጋገጫ ሲሰጠው እንደሆነ ገልጾ ከሆነ፣ ተቀባይ መልዕክቱ ስለመድረሱ የላከው ማረጋገጫ ለአመንጪው እስከሚደርሰው ድረስ መልዕክቱ እንዳልተላከ ተደርጎ ይቆጠራል።

፫/ ማረጋገጫው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወይም በተደረገው ስምምነት መሠረት ለአመንጪው ካልደረሰ፣ ወይም የጊዜ ገደብ ካልተቀመጠ፣ ወይም ጊዜን አስመልክቶ የተደረሰ ስምምነት ከሌለ ተገቢ ነው ተብሎ በሚቆጠር ጊዜ ውስጥ ማረጋገጫው ካልደረሰ፣ አመንጪው፦

ሀ) ከተቀባይ መልዕክቱን ስለመቀበሉ የሚያረጋግጥ መተማመኛ ያልደረሰው መሆኑን ሊያሳውቀው እና ይህን ማረጋገጫ በተወሰነ ቀን ገደብ ውስጥ እንዲደርሰው ግዴታ ሊያስቀምጥ፣ እና

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ አመንጪው ከመልዕክት ተቀባዩ ማረጋገጫ ያልደረሰው ከሆነ ለተቀባዩ ቀድሞ የላከለት የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ፈጽሞ አልተላከም ብሎ እንዲቆጥር ማስታወቂያ ሊሰጠውና፣ ያሉትን ሌሎች መብቶቹን ሊጠቀም ይችላል።

፬/ አመንጪው ከተቀባይ መልዕክቱን ስለመቀበሉ የሚያረጋግጥ መተማመኛ ከተቀበለ የመልዕክቱ ተቀባይ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱን እንደተቀበለ ተደርጎ ግምት ይወሰዳል።

፭/ ማረጋገጫው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ሁለቱ ወገኖች የተስማሙበትን ወይም ደረጃውን በጠበቀ መመዘኛ ተለይተው የተቀመጡ ቴክኒካዊ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆኑን ከገለጸ እነዚህ የተቀመጡ መስፈርቶች እንደተሟሉ ይገመታል።

a) any communication by the addressee, automated or otherwise; or

(\b) any conduct of the addressee sufficient to indicate to the originator that the electronic message has been received.

2/ Where the originator states that the electronic message shall be valid on receipt of the acknowledgement by the addressee, the electronic message is deemed as though it has never been sent until the acknowledgement is received.

3/ Where the acknowledgement has not been received by the originator within the time specified or agreed or, if no time has been specified or agreed, within a reasonable time, the originator:

a) may inform the addressee that no acknowledgement has been received and specify a reasonable time by which it shall be sent; and

b) if the acknowledgement of receipt is not received in a period specified in paragraph (a) of this Sub-Article, give notice to the addressee to treat the electronic message as though it had never been sent and exercise any other rights he may have.

4/ Where the originator receives the addressee's acknowledgement of receipt, it is presumed that the addressee has received the related electronic message.

5/ Where the received acknowledgement states that the related electronic message meets technical requirements, either agreed upon or set forth in applicable standards, it is presumed those requirements have been met.

https://chilot.me



**፳፩. የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች የመላኪያ እና የመቀበያ ጊዜና ቦታ**

፩/ በመልዕክት አመንጪውና በተቀባዩ መካከል በሌላ መንገድ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ተልኳል የሚባለው መልዕክቱ ከመረጃ አመንጪው ወይም ከወኪሉ ውጪ በሆነ የመረጃ ሥርዓት ውስጥ ሲገባ ነው።

፪/ በመልዕክት አመንጪውና በተቀባዩ መካከል በሌላ መልክ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ከተቀባዩ ዘንድ ስለመድረሱ በሚከተለው አግባብ ይረጋገጣል፡-

ሀ) የመልዕክት ተቀባዩ የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን ለመቀበል ሲል የለየው የመረጃ ሥርዓት ካለ መረጃው ደርሷል የሚባለው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ በዚህ የመረጃ ሥርዓት ውስጥ ሲገባ፣ ወይም ተቀባዩ መልዕክቱን ለመቀበል ባልለየው የመረጃ ሥርዓት በኩል የተቀበለ ከሆነ፣ ወይም

ለ) ተቀባዩ መልዕክት የሚቀበልበትን የመረጃ ሥርዓት ለይቶ ካላስቀመጠ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ደርሶታል የሚባለው የተቀባዩ ኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ውስጥ ሲገባ ነው።

፫/ በመልዕክት አመንጪውና በተቀባዩ መካከል በሌላ መልክ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ከአመንጭው የሥራ ቦታ ተልኳል ተብሎ የሚወሰደውና በተቀባይ የሥራ ቦታ ደርሷል የሚባለው፣ ከዚህ በታች ባለው አኳኋን ሲቀርብ ነው፡-

ሀ) የመልዕክቱ አመንጪ ወይም ተቀባዩ ከአንድ በላይ የሥራ ቦታ ያለው ከሆነ በሁለቱ መካከል ከሚካሄደው ትራንዛክሽን ጋር የቀረበ ግንኙነት ያለው የሥራ ቦታ፣ ወይም ይህ ለግንኙነቱ መሠረት የሆነው ትራንዛክሽን ከሌለ ዋናው የሥራ ቦታ እንደ ግባብነቱ የመልዕክቱ የመላኪያ ወይም የመቀበያ ቦታ ተደርጎ ይወሰዳል፣ ወይም

ለ) የመልዕክቱ አመንጪ ወይም ተቀባዩ የሥራ ቦታ የሌለው ከሆነ የመኖሪያ ቦታው እንደ ሥራ ቦታ ያገለግላል።

**21. Time and Place of Dispatch, and Receipt of Electronic Message**

1/ Unless otherwise agreed between the originator and the addressee, the dispatch of an electronic message occurs when it enters an information system outside the control of the originator or its agent.

2/ Unless otherwise agreed between the originator and the addressee, the time of receipt of an electronic message is proved as follows:

a) if the addressee has designated an information system for the purpose of receiving electronic messages, receipt occurs when the electronic message enters the designated information system; or whenever the addressee receives it when it was sent through the electronic system that is not the designated system; or

b) if the addressee has not designated an information system, the electronic message is received when it enters the electronic system of the addressee.

3/ Unless otherwise agreed between the originator and the addressee, an electronic message shall be deemed to be dispatched at the originator's place of business, and received at the addressee's place of business as provided herein below:

a) if the originator or the addressee has more than one place of business, the place of business is that which has the closest relationship to the underlying transaction or, where there is no underlying transaction, the principal place of business; or

b) if the originator or the addressee does not have a place of business, reference is to be made to its habitual residence.

https://chilot.me



**፳፪. የለውጥ ወይም የስህተት ውጤት**

፩/ የኤሌክትሮኒክ መልዕክት በሚተላለፍበት ወቅት ለውጥ ወይም ስህተት ተፈጸሟል የሚባለው የመልዕክት አመንጪው እና ተቀባዩ አንድን የደህንነት ሥርዓትን ጥቅም ላይ ለማዋል የተስማሙ ከሆነና አንደኛው ወገን ይህን ሥርዓት ተከትሎ ካልፈጸመ ነው።

፪/ ለውጥ ወይም ስህተት የፈጸመ አካል ለተቀየረው ወይም ለተሳሳተው የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ተጠያቂ ነው።

፫/ የመልዕክት አመንጪ ወይም ተቀባይ ተጠያቂ የማይሆነው ስህተቱ በወኪሉ የተፈጸመ ከሆነና ወኪሉ ስህተቱ እንዲታረም ዕድል ያላመቻቸ ከሆነ ነው።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው መሠረት የተከሰተን ስህተት የተገነዘበ አካል፦

ሀ) ስህተቱን ወይም ለውጡን ወዲያውኑ ሌላው ሰው እንዲያውቀው ማድረግ እና ለተቀበለው መልዕክት ተጠያቂ እንደማይሆን ማሳወቅ አለበት፤ እንደዚሁም

ለ) ሌላው ወገን የሚሰጣቸውን ምክንያታዊ የሆኑ ትዕዛዞች ማክበርን ጨምሮ በተሳሳተው መልዕክት መሠረት ያገኘውን ጥቅም የመመለስ፣ የመደምሰስና ሌሎች ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባዋል።

**ንዑስ ክፍል ሶስት**

**የመሐል አገናኞች የተጠያቂነት ገደብ**

**፳፫. አስተላላፊ**

፩/ የመሐል አገናኝ ኢንፎርሜሽን የማስተላለፍ አገልግሎቶች በሚሰጥበት ጊዜ ወይም ለቀጥታ መስመር ይፋዊ ግንኙነት ተደራሽነት በሚሰጥበት ጊዜ፦

ሀ) የቀጥታ መስመር ግንኙነቱን የማይቆጣጠር፤

ለ) ስርጭቱን የማያመነጭ፤

**22. Effect of Change or Error**

1/ A change or error occurs in the transmission of an electronic message if the originator and the addressee have agreed to use a security procedure for electronic message and one of them has not conformed to the procedure.

2/ The party who commits the change or error shall be held accountable for the changed or erroneous electronic message.

3/ If an individual is either the originator or the addressee of an electronic message, he shall not be held accountable where the error was made by an individual dealing with an agent if that agent did not provide an opportunity to correct the error.

4/ For the purpose of Sub-Article (1) of this Article, the person noticing an error shall:

a) promptly notify the other person of the error that he is not expectedly held responsible for the message received; and

b) take reasonable steps, including steps that conform to the other person's reasonable instructions, to return to the other person or, to destroy the consideration received, as a result of the erroneous electronic message.

**SUB-SECTION THREE**

**LIMITATIONS ON THE LIABILITIES OF INTERMEDIARIES**

**23. Mere Conduit**

1/ An intermediary shall not, when supplying services of transmission of information, or when offering access to online public communication, be held liable for the information transmitted on condition that the intermediary does not:

a) monitor the online communication;

b) initiate the transmission;

https://chilot.me



ሐ) የስርጭቱን ተቀባይ የማይመርጥ፤ ወይም

መ) በስርጭቱ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች የማይመርጥ ወይም የማይቀይር፤

ከሆነ ለተላለፈው መረጃ ተጠያቂ አይሆንም።

፪/ ኢንፎርሜሽን የማስተላለፍ፣ የመላክ እና ተደራሽ የማድረግ ተግባር የአውቶማቲክን፣ የኮምፒውተር ሥርዓት የሂደት ደረጃዎችን እና ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ጊዜያዊ ክምችትን የሚያካትተው፦

ሀ) ስርጭቱን በመረጃ ሥርዓት ውስጥ ለመልቀቅ ብቻ ከሆነ፤

ለ) ስርጭቱ መልዕክት ተቀባይ ነው ተብሎ ከሚገመተው ሰው ውጭ ለሌላ ሰው ተደራሽ እንዳይሆን ተደርጎ ከተለቀቀ፤ እና

ሐ) ለስርጭቱ ከሚያስፈልገው በላይ ለማይቆይ ጊዜ የሚከማች ከሆነ፤ ነው።

## ፳፬. ይዞ ማቆየት

የመሐል አገናኙ የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ይዞ የሚያቆየው የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱን ለማግኘት ለጠየቁ ተቀባዮች መልዕክቱን ይበልጥ ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ ለማስተላለፍ ከሆነ፤ እንደዚሁም፦

1/ የኤሌክትሮኒክ መዝገቡን ካልቀየረው፤

2/ የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ተደራሽነት ሁኔታዎችን ካከበረ፤

3/ የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ወቅታዊ ማድረግን በተመለከተ በኢንዱስትሪው ውስጥ በስፋት ዕውቅና ካገኙና ጥቅም ላይ ከዋሉ ደንቦች ጋር የሚስማማ ከሆነ፤

4/ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ዙሪያ መረጃ ከማግኘት ጋር በተያያዘ፣ በኢንዱስትሪው በስፋት ተቀባይነት ካገኘና ጥቅም ላይ ከዋለ ሕጋዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር የማይጣረስ ከሆነ፤ እና

c) select the receiver of the transmission; or

d) select or modify the information contained in the transmission.

2/ The acts of transmission, routing and provision of access include the automatic, intermediate and transient storage of the information transmitted in so far as this takes place:

a) for the sole purpose of carrying out the transmission in the information system;

b) in a manner that makes it ordinarily inaccessible to anyone other than an anticipated recipient; and

c) for storage for a period not longer than is reasonably necessary for the transmission.

## 24. Caching

An intermediary shall not be liable for the automatic, intermediate and temporary storage of that electronic record, in case the intention of such a storage of electronic record is to make the onward transmission of the electronic message more efficient to other recipients who requested for it, as long as the intermediary:

1/ does not modify the electronic record;

2/ complies with the conditions for access to the electronic record;

3/ complies with rules regarding the updating of the electronic message, specified in a manner widely recognized and used by the industry;

4/ does not interfere with the lawful use of technology widely recognized and used by the industry, to obtain information relating to the use of the electronic message; and

https://chilot.me


5/ የኤሌክትሮኒክ መረጃውን እንዲያስወግድ ወይም ተደራሽ እንዳይሆን ጥያቄ ሲቀርብለት ይህንኑ የሚፈጽም ከሆነ፤

የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱን በአውቶማቲክ፣ በኮምፒውተር ሥርዓቱ የሂደት ደረጃዎች እና ለአጭር ጊዜ በማከማቸቱ ተጠያቂ አይሆንም።

## ፳፭. ማስቀመጥ

፩/ የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ክምችትን የሚያካትት አገልግሎት የሚያቀርብ የመሐል አገናኝ ከኢንፎርሜሽን ክምችት ጋር ተያይዞ ለሚነሳ ጉዳት፡-

ሀ) ኢንፎርሜሽኑ ወይም ከኢንፎርሜሽኑ ጋር የተያያዘው ተግባር የሶስተኛ ወገን መብትን የሚጥስ መሆኑን ካላወቀ፤

ለ) የተከማቸውን ኢንፎርሜሽን ሕገ-ወጥ ባህርይ ካወቀ በኋላ ወዲያውኑ ኢንፎርሜሽኑን የማውጣት ወይም እንዲህ ዓይነቱን ኢንፎርሜሽን ማግኘት እንዳይቻል የማድረግ እርምጃ ከወሰደ፤ ወይም

ሐ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ኢንፎርሜሽኑን እንዲያወርድ ማስታወቂያ ሲደርሰው ኢንፎርሜሽኑን ለማስወገድ ወይም ተደራሽ እንዳይሆን ለማድረግ በፍጥነት እርምጃ ከወሰደ፤

ተጠያቂ አይሆንም።

፪/ ጥሰት የተፈጸመ መሆኑን በተመለከተ የሚሰጡ ማስታወቂያዎችን እንዲቀበልለት ተወካይ ካልሰየመ እና በሚሰጠው አገልግሎት በኩል በድረ-ገጹ ላይ ጭምር ለህዝብ ተደራሽ በሆኑ ስፍራዎች የተወካዩን ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ ካላሳወቀ በስተቀር፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገጉት የተጠያቂነት ገደቦች በአገልግሎት ሰጪው ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

፫/ የአገልግሎቱ ተቀባይ ከአገልግሎት አቅራቢው ጋር ሆኖ የሚሰራ ከሆነ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተፈጻሚ አይሆንም።

5/ removes or disables access to the electronic message it has stored upon receiving a take-down notice.

## 25. Hosting

1/ An intermediary that provides a service comprising the storage of electronic message shall not be liable for damages arising from information stored, as long as:

a) it is not aware that the information or the activity relating to the information infringes the right of third parties;

b) immediately after becoming aware of the unlawful character of the stored information, it took all necessary measures to withdraw the information or to make access to such information impossible; or

c) upon receipt of a take-down notification provided by this Proclamation acts expeditiously to remove or to disable access to the information.

2/ The limitations on liability established under Sub-Article (1) of this Article do not apply to a service provider unless it has designated an agent to receive notifications of infringement and has provided through its services, including on its website in locations accessible to the public, the name, address, phone number and email address of the agent.

3/ Sub-Article (1) shall not apply if the recipient of the service works with the service provider.

https://chilot.me



## ፳፮. ኢንፎርሜሽን የማግኛ መሳሪያዎች

የመሐል አገናኝ ተገልጋዮችን የሶስተኛ ወገኖችን መብት ወደሚጥሱ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች ወይም የጥሰት ተግባራትን ወደያዙ ድረ-ገጾች የሚያመላክት ወይም ከእነዚህ ድረ ገጾች ጋር የሚያገናኝ ከሆነ፦

፩/ ኢንፎርሜሽኑ ወይም ከኢንፎርሜሽኑ ጋር የተያያዘው ተግባር የሶስተኛ ወገኖችን መብት የሚጥስ ስለመሆኑ ግንዛቤ ከሌለው፤

፪/ የተግባሩ እውነታዎች ወይም ከባቢያዊ ሁኔታዎች ላይ ግንዛቤ ከሌለው፤

፫/ የሶስተኛ ወገኖች መብትን አስመልክቶ የኢንፎርሜሽኑ ባህርይ ግልጽ ካልሆነ፤

፬/ ከተግባሩ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያለው የገንዘብ ጥቅም ካላገኘ፤ ወይም

፭/ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ የሶስተኛ ወገን መብቶችን የሚጥስ መሆኑ ከተገለጸለት በኋላ ከኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ጋር የተያያዙ ኢንፎርሜሽኖችን አግባብነት ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲወገዱ ወይም ተደራሽ እንዳይሆኑ ካደረገ፤

ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም።

## ፳፯. የይውረድ ማስታወቂያ ስለመስጠት

፩/ ለሶስተኛ ወገኖች ተደራሽ ከተደረገ ኢንፎርሜሽን ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታውን ለመሐል አገናኙ፣ ለሚመለከተው አገልግሎት ሰጪ፣ ወይም ለሕጋዊ ወኪሉ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

፪/ ቅሬታ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ኢንፎርሜሽኑ እንዲወርድ ከመጠየቅ ባሻገር፦

ሀ) የአቤቱታ አቅራቢውን ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥርና የኢሜል አድራሻ፤

ለ) የአቤቱታ አቅራቢውን የጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክ ፊርማ፤

ሐ) የተጣሱት መብቶች እና ድርጊቱ ሕገወጥ ስለመሆኑ ማብራሪያ፤

## 26. Information Location Tools

An intermediary shall not be liable for damages incurred when it refers or links users to a website containing infringing electronic messages or infringing activities, where:

1/ it is not aware that the information or activity relating to the information infringes the rights of third party;

2/ it is not aware of facts or circumstances of the infringing activity;

3/ the infringing nature of information is not apparent;

4/ it does not receive a financial benefit directly attributable to the infringing activity; or

5/ removes, or disables access to the information relating to the electronic message within a reasonable time after being informed that such electronic message infringes the rights of third parties.

## 27. Take-down Notification

1/ A person who have complaints with regard to information made available to third parties shall notify, in writing, their complaints with regard to the unlawful activity to the intermediary or to the concerned service provider or its designated agent.

2/ Apart from the requesting the information to be taken down in accordance with Sub Article 1 of this Article , the notification shall include:

a) full name, address, telephone number and electronic mail contacts of the complainant;

b) the written or electronic signature of the complainant;

c) rights that have been infringed and justification of the unlawful activity;

https://chilot.me



መ) ክርክሩን ለመፍታት መወሰድ ያለበትን የመፍትሔ እርምጃ፤ እና

ሠ) ያቀረበው ቅሬታና ኢንፎርሜሽን ትክክለኛ እና እውነተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ መግለጫን

ማካተት አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ ማስታወቂያ ሃሰት መሆኑ እየታወቀ የቀረበ ከሆነ ማስታወቂያ አቅራቢው በፈጸመው ድርጊት ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል።

፬/ በሐሰት በቀረበ ማስታወቂያ መሠረት መረጃ የማውረድ ተግባር የፈጸመ የመሐል አገናኝ በኃላፊነት አይጠየቅም።

## ንዑስ ክፍል አራት

## የሸማቾች መብት ጥበቃ

### ፳፰. የሚቀርቡ መረጃዎች

፩/ ሸቀጦችን እና አገልግሎቶችን በኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አማካኝነት የሚያቀርብ አቅራቢ፦

ሀ) ሙሉ ስሙን፣ አድራሻውን፣ የስልክ ቁጥሩን፣ የድረገጽና የኢሜይል አድራሻውን፤

ለ) የዘርፍ ማህበር አባል ከሆነ አባል የሆነበትን የዘርፍ ማህበርና የማህበሩን አድራሻ፤

ሐ) አቅራቢው ተገዥ የሆነለትን የሥነ-ምግባር ደንብና ሸማቹ የሥነ-ምግባር ደንቡን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማግኘት የሚችልበትን አግባብ፤

መ) ሕጋዊ የንግድ ተቋም ከሆነ የምዝገባ እና የፈቃድ ቁጥሮችን፣ የምዝገባ ቦታና የንግድ ተቋሙን ኃላፊዎች ስም፤

ሠ) አቅራቢው ሕጋዊ ሰነዶችን የሚቀበልበትን አድራሻ፤

d) the remedial action required to be taken in order to resolve the dispute; and

e) a statement by the complainant that the information provided is true and correct.

3/ A person who lodges a notification under Sub-Article (1) of this Article knowing that such notification materially misrepresents the facts is liable for damages for wrongful take-down.

4/ An intermediary is not liable for a takedown in response to a wrongful notification.

## SUB-SECTION FOUR

## CONSUMER PROTECTION

### 28. Information to be Provided

1/ A supplier offering goods and services by way of an electronic transaction shall make the following information available to consumers on the website where such goods or services to be offered are hosted:

a) its full name, physical address, telephone number, and website and e-mail address;

b) membership to a commercial body sending the goods and the contact details of that body, if any;

c) any code of conduct to which that supplier subscribes and how the consumer may access that code of conduct electronically;

d) in case of commercial legal entity, its registration and operation numbers, its place of registration, and the names of its managers;

e) the physical address where that supplier will receive legal service of documents;

https://chilot.me



ረ) ሻማቹ ለቀረበለት የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲወስን ለማስቻል በአቅራቢው ስለቀረቡ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ዓበይት ባህሪያት የተሰጠ በቂ መግለጫ፤

ሰ) የትራንስፖርት ወጪዎችን፣ ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎችን ወይም ወጪዎችን ጨምሮ የሸቀጦቹን እና የአገልግሎቶቹን ሙሉ ዋጋ፤

ሸ) ግዥ ለተፈጸመበት ሸቀጥና አገልግሎት ክፍያ የሚፈጸምበት የአገር ውስጥ የባንክ አካውንት ዝርዝርን ጨምሮ የክፍያ መፈጸሚያ መንገድ፤

ቀ) ዋስትናዎችን ጨምሮ ማንኛቸውም ለትራንዛክሽኑ ተፈጻሚ የሚሆኑ ስምምነቶችና እነዚህ ስምምነቶች ሸማቾች በኤሌክትሮኒክ እንዴት ሊያገኙት፣ ሊያከማቹት እና ቅጅ ሊያዘጋጁለት እንደሚችሉ የሚገልጽ ማብራሪያ፤

በ) ሸቀጦቹ ለሸማች የሚላኩበት እና አገልግሎቶቹ ለሸማች የሚደርሱበት ጊዜን፤

ተ) ሸማቾች የግብይቱን ሙሉ መረጃ ማግኘት የሚችሉበት ጊዜ እና ሁኔታ፤

ቸ) የተሸጠ ዕቃን ስለመመለስ፣ ስለመለወጥ እና የተፈጸመን ክፍያ ተመላሽ ማድረግን በሚመለከት አቅራቢው የሚከተለው ፖሊሲ፤

ኀ) አቅራቢው ተገዥ የሆነለት አማራጭ የግጭት መፍቻ ደንብ እና ሸማቹ የዚህን ደንብ ዝርዝር ይዘት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማግኘት የሚችልበት አግባብ፤

ነ) ከክፍያና የሸማቹ ግላዊ መረጃ ጋር በተያያዘ አቅራቢው የሚከተለው የደህንነት ሥርዓቶች እና የሚስጥራዊነት ፖሊሲ፤ እና

ኘ) እንደ አስፈላጊነቱ የሸቀጦችና የአገልግሎቶች አቅርቦት ቀጣይነት ባለው አኳኋን እንዲሆን ስምምነት ተደርጎ ከሆነ ስምምነቱ ጸንቶ የሚቆይበት አነስተኛው ጊዜ፤

f) a sufficient description of the main characteristics of the goods and services offered by that supplier to enable a consumer to make an informed decision on the proposed electronic transaction;

g) the full price of the goods and services, including transport costs, taxes and any other fees or costs;

h) the mode of payment, including the details of its local bank account where payment for goods and services sold should be made;

i) any terms of agreement, including any guarantees, that will apply to the transaction and how those terms may be assessed, stored and reproduced electronically by consumers;

j) the period of time within which the goods will be dispatched or delivered or within which the services will be rendered;

k) the manner and period within which consumers can access a full record of the transaction;

l) the return, exchange and refund policy of that supplier in respect of goods and payment;

m) any alternative dispute resolution code to which that supplier subscribes and how the details and or contents of that code may be accessed electronically by the consumer;

n) the security procedures and privacy policy of that supplier in respect of payment and personal data of the consumer; and

o) where appropriate, the minimum duration of the agreement in case of agreements for the supply of products or services to be performed on a continuous basis or on a short period of time;

https://chilot.me



የሚገልጽ ኢንፎርሜሽን ለሸማቹ ሸቀጦቹና አገልግሎቶቹ በሚቀርብበት ድረገጽ ላይ ማስቀመጥ ይኖርበታል።

፪/ አቅራቢው ለሸማቾች፡-

ሀ) ሙሉ የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽኑን እንዲገመግሙ፤

ለ) ስህተቶችን እንዲያስተካክሉ፤ እና

ሐ) የግዥ ትዕዛዝ ከመስጠታቸው አስቀድመው ትራንዛክሽኑን ትተው እንዲወጡ፤ ዕድል መስጠት አለበት።

፫/ አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አቀጽ (፩) እና (፪) የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ካላሟላ ሸማቹ ሸቀጦቹን እና አገልግሎቶችን በተቀበለ ፲፬ ቀናት ውስጥ ትራንዛክሽኑን ሊሰርዘው ይችላል።

፬/ ትራንዛክሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ከተሰረዘ፡-

ሀ) ሸማቹ ከአቅራቢው የመጣለትን ምርት ይመልሳል፤ ወይም እንዳግባብነቱ የቀረበለትን አገልግሎት መጠቀም ያቆማል፣

ለ) አቅራቢው የተፈጸመውን ሙሉ ክፍያ ተመላሽ ያደርጋል።

፭/ አቅራቢው ትራንዛክሽኑ ለተካሄደበት ጊዜና ለትራንዛክሽኑ የሚመጥን፣ ተቀባይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ደህንነቱ በሚገባ የተረጋገጠ የክፍያ ሥርዓት ይተገብራል።

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣቱ በሸማቹ ላይ ጉዳት ቢደርስ አቅራቢው ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ነው።

## ፳፱. <u>ውል ማቋረጥ</u>

፩/ የሸቀጦቹን ባህርይ ታሳቢ በማድረግ ሸማቹ ያለ ምንም ምክንያት እና ቅጣት ዕቃውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ባሉ በሰባት (፯) ቀናት ውስጥ ወይም አገልግሎቶቹን መቀበል ከጀመረበት በኋላ ባሉት ሰባት (፯) ቀናት ውስጥ የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽኑን ሊሰርዘው ይችላል።

2/ The supplier shall provide a consumer with an opportunity:

a) to review the entire electronic transaction;

b) to correct any mistakes; and

c) to withdraw from the transaction, before finally placing any order.

3/ If a supplier fails to comply with the Sub-Article (1) and (2) of this Article the consumer may cancel the transaction within 14 days of receiving the goods or services under the transaction.

4/ If a transaction is cancelled as per Sub-Article (3) of this Article:

a) the consumer shall return the performance of the supplier or, where applicable, cease using the services provided; and

b) the supplier shall refund all payments made by the consumer less the direct cost of returning the goods.

5/ The supplier shall utilize a payment system that is sufficiently secure with reference to accepted technological standards at the time of the transaction and the type of transaction concerned.

6/ The supplier shall be liable for any damage suffered by a consumer due to its failure to comply with Sub-Article (5) of this Artice.

## 29. <u>Termination of Contract</u>

1/ Depending upon the nature of the goods delivered, a consumer may cancel without reason and penalty an electronic transaction and any related credit agreement for the supply of goods within seven (7) days after the date of the receipt of the goods; or of services within seven (7) days after the date he started to receive the services.

https://chilot.me



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ተፈጻሚ ሲሆን በሸማቹ ላይ ሊጣል የሚገባው ክፍያ ሸቀጡን ተመላሽ ለማድረግ የሚወጣ ቀጥተኛ ወጪ ብቻ ነው፡፡

፫/ ሸማቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸውን መብት ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት ለሸቀጦቹ ወይም ለአገልግሎቶቹ ክፍያ ፈጽሞ ከሆነ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው ወጪ ከሙሉ ክፍያው ላይ ተቀናሽ ተደርጎ የማስመለስ መብት አለው፤ ክፍያው ተመላሽ የሚደረግለት ውሉ ከተሰረዘ በኋላ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ ነው፡፡

## ፴. ሸማች ለግዥ ባልጠየቃቸው ጉዳዮች ዙሪያ የሚደረጉ ኮሙኒኬሽኖች

፩/ ጥያቄ ባልቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ የንግድ ኮሙኒኬሽኖችን ለሸማቾች የሚልክ ማንኛውም ሰው፣ ሸማቹ ስሙ ከዚህ ሰው የመልዕክት ተቀባዮች ዝርዝር ውስጥ እንዲሰረዝ አማራጭ ሊያቀርብለት ይገባል፡፡

፪/ ጥያቄ ባልቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ የንግድ ኮሙኒኬሽኖችን ለሸማቾች የሚልክ ማንኛውም ሰው፣ ሸማቹ ሲጠይቀው የሸማቹን ግላዊ ኢንፎርሜሽን ያገኘበትን ምንጭ መስጠት አለበት፡፡

፫/ ሸማቹ ጥያቄ ባላቀረበበት ጉዳይ ላይ ለቀረበለት የንግድ ኮሙኒኬሽኖች ምላሽ ካልሰጠ በሁለቱ መካከል ስምምነት እንደተፈፀመ ተደርጎ አይወሰድም፡፡

## ፴፩. የውል አፈፃፀም

፩/ ተዋዋይ ወገኖች ከዚህ በተቃራኒ ካልተስማሙ በስተቀር አቅራቢው ትዕዛዙን ከተቀበለበት ቀን አንስቶ ባሉት በሰላሳ (፴) ቀናት ውስጥ ትዕዛዙን መፈፀም አለበት፡፡

፪/ አቅራቢው ትዕዛዙን በ፴ ቀናት ውስጥ ወይም በሌላ በተስማሙበት ጊዜ ውስጥ ካልፈፀመ ሸማቹ እነዚህ የውል መፈፀሚያ ጊዜዎች እንደተጠናቀቁ የሰባት ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስምምነቱን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

2/ The only charge that may be levied on the consumer in those cases under Sub-Article (1) of this Article is the direct cost of returning the goods.

3/ If payment for the goods or services has been effected prior to a consumer exercising a right referred to in Sub-Article (1) of this Article, the consumer shall be entitled to a full refund of such payment minus the amount due as provided in Sub-Article (2) of this Article, which refund shall be made within thirty (30) days from the date of cancellation.

## 30. Unsolicited Communications

1/ A person who sends unsolicited commercial communications to consumers shall provide the consumer with the option to cancel his subscription from the mailing list of that person.

2/ A person who sends unsolicited commercial communications to consumers shall provide upon request by the consumer the particulars of the source from which he obtained the consumer's personal information.

3/ No agreement is concluded where a consumer has failed to respond to an unsolicited communication.

## 31. Contract Performance

1/ Unless the parties have agreed otherwise, the supplier shall execute the order within thirty (30) days after the day on which it received the order.

2/ Where a supplier has failed to execute the order within 30 days or within the agreed period, the consumer may after the expiration of that period cancel the agreement with seven days' written notice.

https://chilot.me



፫/ አቅራቢው ለማቅረብ የተስማማባቸው ሸቀጦች ወይም አገልግሎቶች የማይገኙ ከመሆናቸው የተነሳ የስምምነት ግዴታዎቹን መፈፀም ካልቻለ ይህንኑ እውነታ ለሸማቹ ወዲያውኑ በማሳወቅ ሸማቹ የፈፀመውን ማንኛውንም ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ ተመላሽ ማድረግ አለበት።

## ፴፪. የውጭ አገራት ሕጎች ተፈፃሚነት

ተዋዋዮች ስምምነታቸው የሚገዛበትን የሕግ ሥርዓት አስመልክቶ የተስማሙባቸው ስምምነቶች የትኛውም ይሁኑ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከተው የሸማቾች ጥበቃ ድንጋጌዎች ገዥ ናቸው።

## ፴፫. ቀሪ የማይደረጉ መብቶች

፩/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱትን መብቶች አጠቃቀም የሚያስቀር ማንኛውም የስምምነት ውል ዋጋ አይኖረውም።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በሌላ በማንኛውም ሕግ ውስጥ ለሸማቾች የተሻለ መብት የሚሰጡ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ፴፬. አቤቱታ ስለማቅረብ

ሸማቹ በአቅራቢው በኩል የተፈፀሙ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚጻረሩ ድርጊቶችን አስመልክቶ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል።

## ንዑስ ክፍል አምስት

## የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች

## ፴፭. ሰነድን በኤሌክትሮኒክ መቀበልና መስጠት

፩/ በሕግ መሠረት ሰነዶችን የሚቀበል፣ የሚያዘጋጅ፣ የሚያስቀምጥ፣ ፈቃድ የሚሠጥ፣ የክፍያ ሥርዓት የዘረጋ ማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም ሰነዶችን፣ ፈቃዶችን፣ ወይም የክፍያ ሥርዓቶችን በኤሌክትሮኒክ ቅርጽ ወይም መንገድ ሊቀበል፣ ሊያዘጋጅ እና ሊሰጥ ይችላል።

3/ If a supplier is unable to comply with the terms of agreement on the grounds that the goods or services ordered are unavailable, the supplier shall immediately notify the consumer of this fact and refund any payments made by consumer within seven days after the date of such notification.

## 32. Applicability of Foreign Law

The Section on Consumer Protection provided for in this Proclamation applies irrespective of the legal system applicable to the agreement in question.

## 33. Non-Exclusion

1/ Any provision in an agreement which excludes any rights provided for in this Proclamation is null and void.

2/ the rights of a consumer provided for in any other law which give the consumer a better protection shall find application not withstanding Sub-Article (1) of this Article.

## 34. Complaints

A consumer may lodge a complaint with the Ministry in respect of any non-compliance with the provisions of this Proclamation by any supplier.

## SUB-SECTION FIVE

## ELECTRONIC GOVERNMENT SERVICES

## 35. Acceptance of Electronic Filing and Issuing of Documents

1/ Any government agency that, pursuant to any law accepts the filing of documents, or requires that documents be created or retained; issues any permit, license or approval; or provides for a manner of payment, shall, notwithstanding anything to the contrary in such law, accept the filing of such documents, or the creation or retention of such documents in the form of electronic messages; issue such permit, license or approval in the form of an electronic message or make or receive payment in electronic form or by electronic means.

https://chilot.me



፪/ አንድ የመንግስት ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን ተግባራት ሲያከናውን፦

ሀ) የመዝገብ አያያዝ ሁኔታ፣ የሰነዶች ቅርጽ እና መልዕክቶች የሚሰራጩበትን አግባብ፤

ለ) በኤሌክትሮኒክ ሰነድ ላይ ፊርማ የሚያርፍበትን ቦታ እና ጥቅም ላይ የሚውለውን የፊርማ ዓይነት፤

ሐ) የኤሌክትሮኒክ ፊርማ የሚያርፍበትን አግባብና ዘዴ እና በሰርተፊኬት ሰጪ ባለሥልጣን ከተቀመጠው ሁኔታ ጋር የማይቃረኑ ተፈላጊ መስፈርቶች፤

መ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶችን ትክክለኛነትና ዋና ቅጅ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና በአስተማማኝ ሁኔታ ተጠብቀው የሚቆዩበትን ሁኔታ ለመፈተሽ ጥቅም ላይ የሚውል ሥርዓት፤ እና

(ሠ) ከላይ ከተጠቀሱት ሰነዶች ጋር የተገናኘ ለኤሌክትሮኒክ መልዕክት እና የክፍያ ዘዴዎች ጠቃሚ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ሌሎች አስፈላጊ ክፍሎችን፤

ለይቶ በዝርዝር ሊወስን ይችላል።

፫/ የመንግስት ተቋማት ለኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች እና ለኤሌክትሮኒክ ፊርማዎች አጠቃቀም የላቀ የደህንነት መስፈርቶችን መጠቀም አለባቸው።

፬/ የመንግስት ተቋማት ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ውስጥ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶችን መስጠት መጀመር አለባቸው።

**፴፮. <u>የፌደራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ መቋቋም</u>**

፩/ የፌደራል የሕግ ጋዜጣ የሆነ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የሚወጣ የፌደራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፦

ሀ) ማንኛውም የፌደራል መንግሥት ሕግ የሚወጣው በፌደራሉ የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ ነው፤

2/ Where a public body performs any of the functions referred to in Sub-Article (1) of this Article, such body may specify:

a) mode of archiving, its format and its transmission modalities;

b) space for signature on the electronic document and type of electronic signature to be used;

c) manner and method of affixing electronic signature and requirements not contrary to conditions set by the certification authority;

d) the system to check the authenticity and originality of electronic messages as well as their safe retention; and

e) any other element deemed useful to the electronic message and modes of payments relating to above-mentioned documents.

2/ Public bodies shall use advanced security requirements for the use of electronic messages and electronic signatures.

3/ Public bodies shall start to roll out providing electronic services within a year of the date this Proclamation comes into effect.

**36. <u>Establishment of the Federal Electronic Negarit Gazeta</u>**

1/ The Federal Electronic Negarit Gazeta, a Federal Law Electronic Gazette published under the umbrella of the House of Peoples' Representatives, is hereby established.

2/ Without prejudice to Article 2 of the Federal Negarit Gazeta Proclamation;

a) all laws of the Federal Government shall be published in the Federal Electronic Negarit Gazeta;

https://chilot.me



ለ) ማንኛውም የፌደራል እና የክልል ሕግ አውጪ፣ አስፈጻሚ፣ እና ተርጓሚ እንዲሁም ማንኛውም ሰው በፌደራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጣ ሕግን የመቀበል ግዴታ አለበት፤

ሐ) የፌደራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ የሚታተመው በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ነው፤ በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል የይዘት ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ የአማርኛው የበላይነት ይኖረዋል።

፫/ ማንኛውም ሕግ በፌዴራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ይወጣል።

**፴፯. <u>የፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ መቋቋም</u>**

፩/ የፌደራል የሕግ ጋዜጣ የሆነ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የሚወጣ የፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፦

ሀ) ማንኛውም የፌደራል አስፈጻሚ አካላት የሚያወጧቸው መመሪያዎች የሚወጡት በፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ ነው፤

ለ) ማንኛውም የፌደራል እና የክልል ሕግ አውጪ፣ አስፈጻሚ፣ እና ተርጓሚ እንዲሁም ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ የሚወጣ ሕግን የመቀበል ግዴታ አለበት፤

ሐ) የፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ የሚታተመው በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ነው፤ በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል የይዘት ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ የአማርኛው የበላይነት ይኖረዋል።

፫/ መመሪያዎች በፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ ታትሞ የወጡበት ቀን ሕጉ የታተመበት ቀን እንደሆነ ይቆጠራል።

፬/ የኢኖቬሽንና የቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብን ቴክኒካዊ ጉዳዮች ያስተዳድራል።

b) all Federal and Regional Legislative, Executive and Judicial Organs as well as any person shall take judicial notice of laws published in the Federal Electronic Negarit Gazeta; and

c) the Federal Electronic Negarit Gazeta shall be published in both the Amharic and English languages; in case of discrepancy between the two versions the Amharic shall prevail.

3/ any law is published in the Federal Electronic Negarit Gazeta

**37. <u>Establishment of the Federal Electronic Register of Laws</u>**

1/ The Federal Electronic Register of Laws, a Federal Law Electronic Gazette published under the umbrella of the House of Peoples' Representatives, is hereby established.

2/ Without prejudice what is provided under Article 2 of the Federal Negarit Gazeta Proclamation;

a) the Federal Electronic Register of Laws publishes, directives of the Federal executive body;

b) all Federal and Regional Legislative, Executive and Judicial Organs as well as any natural or juridical person shall take judicial notice of subsidiary laws published in the Federal Electronic Register of Laws;

c) the Federal Electronic Register of Laws shall be published in both the Amharic and English languages; in case of discrepancy between the two versions the Amharic shall prevail.

3/ The date of publication of directives in the Federal Electronic Register of Laws shall be deemed to be the date of publication

4/ The Ministry of Innovation and Technology shall administer the technical aspect of the Federal Electronic Registry of Laws.

https://chilot.me



፭/ በንዑስ አንቀጽ (፬) የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ይችል ዘንድ፣ የፌደራሉ አስፈጻሚ አካላት የሚያወጧቸውን መመሪያዎች፣ ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት የወረቀት እና የኤሌክትሮኒክ ቅጅዎች ለሚኒስቴሩ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፤ እነዚህ ቅጅዎች በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ መቅረብ አለባቸው።

5/ In order for it to fulfill its mandate under Sub-Article (4), government bodies shall have the obligation to provide hard and soft copies of directives to the Ministry, such copies shall be in both the Amharic and English languages.

## ክፍል ሶስት

## የዶሜን ስም ማኔጅመንት

## PART THREE

## DOMAIN NAME MANAGEMENT

### ፴፰. የዶሜን ስም ሬጂስትራር

ባለሥልጣኑ የዶሜን ስም ሬጅስትራር በመሆን ያገለግላል፣ የዶሜን ስም ማኔጅመንት የሥራ ክፍል ይፈጥራል።

### 38. Appointment of the Registrar of Domain Names

The Authority shall serve as the registrar of Domain Name; it shall create a department to administer and manage the ".et" domain name space.

### ፴፱. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ኃላፊነት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ) የኢ.ቲ ዶሜይን ስም ቦታን ያስተዳድራል፣ ይመራል፤

ለ) ለመዝጋቢ ተቋሞች ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ) ለመዝጋቢ ወኪሎች ፈቃድ ይሰጣል ይቆጣጠራል፤

መ) የኢ.ቲ ዶሜይን ስም ቦታን በማስተዳደር ረገድ የተገኙ የተሻሉ ዓለማቀፋዊ ተሞክሮዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) አጠቃላይ የዶት ኢ.ቲ ዶሜይን ስም ቦታ አስተዳደር እና ማኔጅመንትን፤

ለ) ለዶሜይን ስም ምዝገባ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እና ሥነ-ሥርዓቶችን፤ እና

(ሐ) የምዝገባ ሰነዱ አያያዝና ተጠቃሚዎች ከሰነዱ መረጃ የሚያገኙበት አግባብ፤

በተመለከተ መመሪያዎችን ያወጣል።

### 39. Power and Responsibilities of the Authority

1/ Without prejudice to generality of Article 38 of this proclamation, the Authority shall perform the following functions:

a) administer and manage the .et domain name space;

b) issue license and regulate registries;

c) issue license and regulate registrars for the respective registries;

d) ensure compliance by users with international best practices in the administration of the ".et" domain name space;

2/ Without prejudice Sub-Article (1) of this Article, the Authority shall publish directives on:

a) the general administration and management of the ".et" domain name space;

b) the requirements and procedures for domain name registration; and

c) the maintenance of, and public access to, the registry.

https://chilot.me



፫/ ባለሥልጣኑ የዶሜይን ስም ምዝገባ በሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ ይሠራል።

፬/ ባለሥልጣኑ ከዶሜይን ስም ቁጥጥር ጋር በተያያዘ፡-

ሀ) አስፈላጊ ናቸው ብሎ ባመናቸው ጉዳዮች ላይ ምርመራዎችን ሊያካሂድ ይችላል፤

ለ) በአገር ውስጥና በሌሎች አካባቢዎች ከዶሜይን ስም ሥርዓት ጋር በተያያዘ በታዩ ለውጦች ዙሪያ ምርምሮችን ያካሂዳል፤

ሐ) የዶት ኢቲ ዶሜይን ስም የዜጎችን ፍላጎት በምን ያህል ደረጃ እንዳሟላ በቀጣይነት ያጠናል፣ ይገመግማል፤ እና

መ) በኢትዮጵያ የሚካሄድ የዶሜይን ስም ምዝገባን የሚመለከቱ መረጃዎችን ሊያሰራጭ ይችላል።

፭/ ባለሥልጣኑ ይህ አዋጅ ፀድቆ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈጠሩ የዶት ኢቲ ዶሜይን ስም ቦታን የመምራትና የማስተዳደር ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውንም ተቋም መብቶችና ጥቅሞችን ይጠብቃል።

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተጠቀሱት እና በዶት ኢቲ ዶሜይን ማኔጅመንትና አስተዳደር ላይ የራሳቸው መብቶችና ጥቅሞች ያሏቸው ተቋሞች፡-

ሀ) በውክልና በያዟቸው ንዑስ ዶሜይኖች ላይ ለስድስት ወራት ያህል ጊዜ እንዲሠሩ፤ እና

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሰው የስድስት ወር ጊዜ ካበቃ በኋላ በመዝጋቢነት እንዲመደቡ፤

ከሌሎች በተለየ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

3/ The Authority shall enhance public awareness on the economic and commercial benefits of domain name registration.

4/ The Authority, in relation to domain name regulation:

a) may conduct such investigations as it may consider necessary;

b) shall conduct research into and keep abreast of developments in Ethiopia and elsewhere on the domain name system;

c) shall continually survey and evaluate the extent to which the ".et" domain name space meets the needs of the citizens of Ethiopia; and

d) may issue information on the registration of domain names in Ethiopia.

5/ The Authority shall, in relation to the ".et" domain name space existing prior to the coming into force of this Proclamation, uphold the vested rights and interests of any party involved in the management and administration of the ".et" domain name space.

6/ Those parties referred in Sub-Article (5) of this Article and have vested rights and interests in the management and administration of the ".et" domain space shall be:

a) granted a period of six months during which they may continue to operate in respect of their existing delegated sub-domains; and

b) considered, among other persons, for appointment to the post of Registrar after the expiry of the six month period stipulated under this Sub-Article (6) paragraph (a).

https://chilot.me



## ፵. የዶሜይን ስሞችን ያለፈቃድ ማስተዳደር

፩/ ፈቃድ ሳይሰጠው ሁለተኛ ደረጃ የዶሜይን ስምን ያስተዳደረ፣ የመራ ወይም ሥራ ላይ ያዋለ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀው ድርጊት በመፈፀሙ ምክንያት በሶስተኛ ወገን ጥቅም ላይ ጉዳት ደርሶ ከሆነ ወይም ተከሳሹ ድርጊቱን የተፈፀመው ለራሱ ወይም ለሶስተኛ ወገን ያልተገባ ጥቅም ለማስገኘት አስቦ ከሆነ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተጠቀሰው ድርጊት የተፈፀመው በህግ ሰውነት በተሰጠው ተቋም በሆነ ጊዜ እንደ አግባብነቱ ከብር አንድ መቶ ሺ.ህ (100,000 ብር) በማያንስ የገንዘብ ቅጣት የሚያስቀጣ ይሆናል

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፵፩. የአንቀሳቃሾች ግዴታዎች

፩/ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች፣ እና የኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ አንቀሳቃሾች እንደንግድ ተቋማት ዕውቅና ይሰጣቸዋል፤ የንግድ ተቋማት የሚገዙባቸው ሕጎችም በእነሱ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፪/ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች በእነርሱ ፕላትፎርም ላይ ሸቀጦች ወይም አገልግሎቶች ሊያቀርቡ ከሚፈልጉ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ማንነታቸውን ፣ አድራሻና ተዛማጅ መረጃን፣ ፈቃዳቸውን እና ሌሎች መሠል መረጃዎች እንዲያቀርቡላቸው መጠየቅ አለባቸው፤ የእነዚህንም መረጃዎች ትክክለኛነት ማጣራት፣ መመዝገብ፣ መረጃዎቹን በየጊዜው ማስተካከልና ማረም አለባቸው።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ውስጥ በኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ላይ የተጣሉ ግዴታዎች በኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ አንቀሳቃሾች ላይ ተፈፃሚ ናቸው።

## 40. Administering Domain Names without Authority

1/ A person who administers, manages or operates second level domain name without the Permission of the authority shall be punished with simple imprisonment not less than six months.

2/ Due to the commission of the act stated under Sub Article (1) of this Article, if the interst of third party has been affected or it has been committed with the intent to acquire undue benefit for himself/herself or third party the punishment Shall be rigorous imprisonment from one year up to five years.

3/ where the acts stated under Sub Articles 1 and 2 of this Article have been committed by a legal person the punishment shall be a fine note less than one hundred thousand (100,000 ) Ethiopian Birr.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 41. Duties of Operators

1/ Electronic commerce operators, electronic commerce platform operators, and electronic commerce intra-platform operators are recognized as forms of commercial entities and shall be bound by all laws which pertain to running a commercial entity.

2/ Electronic commerce platform operators shall request electronic commerce operators applying for selling commodities or provide services on the platform to submit their true information, such as their identity, address and related contact information and administrative licenses, verify and register the same, set up archives, update and verify regularly.

3/ The duties of electronic commerce platform operators under Sub-Article (2) of this Article shall also apply towards electronic commerce intra-platform operators.

https://chilot.me



፬/ አንቀሳቃሾች ለገበያ ከሚያቀርቧቸው ምርት እና አገልግሎት ውስጥ ፶% የሚያህለው የአገር ውስጥ ምርት እና አገልግሎት መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

፭/ የፈጣን መልዕክት አገልግሎት ሰጪዎች በኤሌክትሮኒክ ግብይት ውስጥ ያላቸው ሚና እውቅና ተሰጥቶታል።

## ፵፪. አለመግባባቶችን የመፍቻ መንገዶች

፩/ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አመቻቾች አለመግባባቶችን የመፍቻ አማራጭ መንገዶች መቀየስ አለባቸው።

፪/ ባለሥልጣኑ የዶሜይን ስም ማኔጅመንትና አስተዳደርን አስመልክቶ አለመግባባቶችን የሚፈታበት አማራጭ መንገዶችን መቀየስ አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች መፍትሔ ያላገኙ አለመግባባቶች በዚህ አዋጅ፣ እና ይህን አዋጅ መሠረት በማድረግ በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች በተመሠረተ የግልግል የዳኝነት ሥርዓት ቀርቦ እልባት ያገኛል።

## ፵፫. ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ

፩/ በዚህ አዋጅ ወይም አግባብነት ባለው በሌላ ሕግ ከተፈቀደላቸው ሰዎች በስተቀር የኤሌክትሮኒክስ መልዕክቶችን፣ ሌሎች የጽሑፍ ሰነዶችን ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን ማግኘት የሚችል ማንኛውም ሰው በዚህ አግባብ ያገኘውን ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

፪/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው የተጣሰ እንደሆነ ድርጊቱ በወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

## ፵፬. ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

4/ Operators shall ensure that local products and services constitute at least 50% of their offer.

5/ The role of express logistic service providers in electronic commerce is recognized

## 42. Dispute Resolution Mechanisms

1/ Electronic commerce platform operators shall establish a dispute settlement mechanism.

2/ With regard to the management and administration of the <.et> domain space, the Authority shall establish a dispute settlement mechanism.

3/ Any unresolved disagreement between parties which fall within the ambit of Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall be submitted to arbitration in accordance with the rules of arbitration of a dispute settlement mechanism established under this Proclamation and the regulations and directives thereunder.

## 43. Obligation of Confidentiality

1/ With the exception of persons authorized by this Proclamation or other relevant law, persons who can access electronic messages, any other written documents or other electronic devices have the obligation to keep them confidential.

2/ In case of Violation of what is stipulated in Sub-Article (1) of this Article, the act shall be punishable according to the provisions of the Criminal Code.

## 44. Inapplicable Laws

Any law which is inconsistent with this Proclamation shall not be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation.

https://chilot.me



፵፭. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የሚወጣ ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር በዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚወጡ ደንቦች በሚመነጩ ጉዳዮች ላይ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

፵፮. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በምክር ቤቱ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ/ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

45. **Powers to Issue Regulations and Directives**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations for the implementation of the Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives for the implementation of this Proclamation and Regulations issued under Sub Article (1) of this Article.

3/ The Authority in consultation with the Ministry may issue directives for the implementation of matters arising from this Proclamation and Regulations thereunder.

46. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force as of the date ratified by the House.

**Done at Addis Ababa, on this 30th day of June, 2020.**

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**